## በትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚ የሚተላለፉ መልእክቶች

## አስመላሽ ወልደማሪያም እና ጽጌረዳ ተክሌ

## ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ

### 1.0 መግቢያ

የለቅሶ አጋጣሚ ሲባል የለቅሶ ግጥሞች የሚደረደሩበትን ወቅት ለማመልከት ነው ። በዚሁም መሰረት የፅሑፉ ትኩረት በለቅሶ አጋጣሚ፥ አጋጣሚውን መሠረት በማድረግ ግጥሞችን በሚደረድሩ አልቃሾችና በሚያስተላልፉዋቸው መልእክቶች ላይ ይሆናል ። በዚህም ስነቃል የአንድን ህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች እንዴት መግለፅ እንደሚችል በመጠኑ ለማሳየት ይሞከራል ።

ስራችንን ለመጀመር መሠረት ያደረግነው በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ በስነቃል ጥናትና ምርምር ቡድን ለትግርኛ ስነቃል ጥናት በተሰበሰቡት ከ1000 በላይ በሆኑ የለቅሶ ግጥሞች ላይ ነው ። አብዛኞቹ ግጥሞች የተሰበሰቡት ከኤርትራና ትግራይ ክፍላተ ሀገር በመስክ ሥራ ሲሆን ጥቂቶቹ ደግሞ አንዳንድ የሃገር ውስጥና የውጭ ሀገር ሰዎች በመፅሃፎቻቸው ካሰፈሩዋቸው የተገኙ ናቸው ።

ግጥሞቹ የተደረደሩበት ዘመን ከአስራ አምስትና ከሃያ ዓመታት በፊት ነው ። ይህም የሆነበት ምክንያት በለቅሶ አጋጣሚዎች ግጥሞችን መደርደር አንዱን አካባቢ ከሌላው አካባቢ ፣ አንዱን መንደር ከሌላው መንደር ሲያጣላና ሲያነታርክ በመታየቱ በክርስትና ሃይማኖት መሪዎች ዘንድ በመወገዙ ባሁኑ ጊዜ እየቀረ በመምጣቱ ነው ። በዚሁም ምክንያት በፅሑፉ ውስጥ የተጠቀሱ አንዳንድ ግጥሞች ከጊዜ ብዛት የተነሳ የአልቃሾቹን ስም ፣ ትክክለኛ ጊዜና ቦታ ለማወቅ ያዳግታል ። ሆኖም ግጥሞቹን የነገሩንን ሰዎች ስምና አጭር መግለጫ በአባሪነት አስፍረናል።

ጽሑፉ ሲዘጋጅ አንዳንድ ችግሮች ገጥመውታል ። ከችግሮቹ አንዱ የትርጉም ችግር ነው ። በመረጃነት የቀረቡ አንዳንድ የትግርኛ ግጥሞችን ቃላትና ሃረጎች ወደ አማርኛ ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው ። ቢሆንም የቃላቱን ፍቺ ከይዘቱ ጋር በማስረዳት ፣ ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር በመወያየት በተቻለ መጠን ትርጉሙን ለማስተካከል ሞክረናል ። በተጨማሪም የሰውና የቦታ ስሞችን ከሌሎች ስሞች ለመለየት እንዲያመች አስምረንባቸዋል ።

ሌላው ችግር አንዳንድ የምንጠቀምባቸው የአማርኛ ቃላት ፍቺ አሻሚ መሆን ነው ። ለዚሁም የተሰጠው መፍትሄ ደስታ ተክለ ወልድ

አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ከሰጡት ፍቺዎች መካከል ለዚህ ጽሑፍ ተስማሚ የሆነውን መውሰድ ነው ።

በዚሁ መሠረት፣

አልቃሽ የሚለውን ቃል የለቅሶ ግጥም ገጣሚ ፣ ደርዳሪ በሚለው ትርጉሙ ተጠቅመንበታል ፣ (ደስታ1962;739)

አለቀሰ የሚለውም የለቅሶ ግጥም ገጠመ ደረደረ በሚለው ፍቺው የተጠቀምንበት ሲሆን ፣ አለቀሰላቸው ፣ አለቀሰችላቸው ወዘተ ስንል ገጠመላቸው ፣ ገጠመችላቸው ማለታችን እን ደሆነ በቅድሚያ ለመግለፅ እንወዳለን ።

ለማስረጃነት የቀረቡት አንዳንድ የትግርኛ ግጥሞችም የግዕዝንና የአማርኛን ቃላት፣ ሀረጎችንና ዐረፍተ ነገሮችን ይደባልቃሉ ። ይህም የትግርኛ የለቅሶ ግጥሞች አንዱ ባህርይ መሆኑን በቅድሚያ ለማስታወስ እንወዳለን ።

## 1.1 የትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚና አልቃሾች

### 1.1.1 የለቅሶ አጋጣሚ

ለስነቃል ህልውና መሰረታዊ ከሆኑት ነጥቦች አንዱ የአጋጣሚ መኖር ነው ። አጋጣሚ ሲባልም አንድን ስነቃል ለመከወን ማለትም ዘፈ ንን ለመዝፈን ፣ ተረትን ለመተረት ፣ ልጅን ለማባበል ወዘተ የሚ ያነሳሳ የሚገፋፋ ምክንያት ማለት ነው ። የሰርግ ዘፈን የሚዘፈነው ሰርግ ሲኖር ነው ፤ የስራ ዘፈኖች የሚዘፈኑት በእርሻ ፣ በአረም ፣ በአጨዳ፣ በአሂዶ ፣ በወፍጮ ወዘተ - ነው ። ሙሾ የሚደረደረውም ሰው ሲሞት ነው ። በአጠቃላይ ለአንድ ስነቃል መፈጠርና ህልውና አጋጣሚው ከፍተኛ ድርሻ አለው ። ለዚህም ነው ስነቃል “ - - - ልደቱ በስራ ፣ በሰርግ ፣ በጋብቻ ስነ ስርዓት ፣ በድል በዓል ፣ በጦርነት ፣ በልጅ ማባበል ወዘተ ነው” የሚባለው ። (ፈቃደ 1972:3)

የለቅሶ አጋጣሚ ሲባልም ሰው ሲሞት ፣ ዘመድ ተሰብስቦ ሲያለቅስ ፣ ችሎታ ያላቸው ሰዎችም ሟች በሕይወት ዘመኑ ያከናወናቸውን ተግባ ራት ፣ የተለያዩ ባህርያቱን ፣ የትውልድ አገሩን ፣ የዘር ሀረጉን ወዘተ በመጠቃቀስ ግጥም የሚደረድሩበት ወቅት ማለት ነው። አልቃሾች ግጥ ሙን የሚደረድሩት ሰውን ሊያስለቅስ እንዲችል አድርጎ በማዜም ነው ።

በትግርኛ ተናጋሪ ብሄረሰብም በለቅሶ አጋጣሚ ግጥሞችን መደር ደር የተለመደ ሲሆን ግጥሞች የሚደረደሩበት የተለያዩ ስነ ስርዓቶች አሉ ። እነዚህም

(ሀ) ቀብር ፡ እንደሚታወቀው ሁሉ ፡ አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወዳጅ ዘመድ ተሰብስቦ እያለቀሰ የአስከሬኑ ግብአተ መሬት የሚ ፈጸምበት ስነስርዓት ነው ። አስከሬኑ ከቤት ወጥቶ ቤተ ክርስቲያን እስኪ ደርስ በሚደረገው የጉዞ ፍታት ስነስርዓት ወቅት ፡ አልቃሾች ግጥሞችን ይደረድራሉ ። ግብአተ መሬቱ ከተፈጸመ በኋላም የሟች ቤተ ሰቦችን ለመ ሰናበት ከሚደረገው ስነ ስርዓት በፊትም አልቃሾች ግጥም ለመደርደር አጋጣሚ ያገኛሉ ።

(ለ) ካልኣይ ቀብሪ ፡ ቀጥተኛ ትርጉሙ ሁለተኛ ቀብር ማለት ሲሆን በትግርኛ ተናጋሪ ብሄረሰብ የተለመደ ስነ ስርዓት ነው ። ይህም ሟች የሞተው ከትውልድ አገሩ ወይም ቤተሰቦቹ ካሉበት ቦታ ርቆ ከሆነና ፡ አስከሬኑም በሞተበት አገር ሲቀበር ወይም ሟች ቤተሰቦቹ ባሉበት ሞቶ ግን ራቅባሉ መንደሮችና ከተሞች የሚገኙ ወዳጅ ዘመዶች ለቀብሩ ሳይ ደርሱ ሲቀሩ እርማቸውን እንዲያወጡ ታስቦ የሚደረግ ስነ ስርዓት ነው ። ይህም ከቀብሩ (የመጀመሪያው) የሚለየው የአስከሬን አለመኖር ብቻ ሲሆን ፡ ለቀብር የሚያስፈልጉና በቀብር የሚደረጉት ስነስርዓቶች ሁሉ በሚገባ ይሟላሉ ።

(ሐ) አርባና ሙት ዓመት ከላይ ከተጠቀሱት የቀብር ስነስርዓቶች ሌላ ሟችን ለማስታወስ በየወቅቱ በሚደረጉ ስነ ስርዓቶች በአርባና በሙ ታመት ላይ አንዳንድ ጊዜ የለቅሶ ግጥሞች ይደረደራሉ ። ስነ ስርዓቱ ሟ ችን ለማስታወስ የሚዘጋጅ ስለሆነ የሚበላውና የሚጠጣው ቀርቦ በቄሶች በኩል የፍታት ፀሎት ከተሰማ በኋላ አልቃሾች ተነስተው ያለቅሳሉ ።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የለቅሶ አጋጣሚ ሞት ሲሆን በትግርኛ ተናጋሪ ብሄረሰብ ይህ አጋጣሚ የተለያዩ ስነ ስርዓቶች አሉት። የኅብረተሰቡ አባላት የሆኑ አልቃሾችም ባላቸው ችሎታ አጋጣሚውን ለመጠቀም በልቅሶ ሃሳባቸውን ይገልፃሉ ።

### 1.1.2 አልቃሽ

ለስነቃል ህልውና መሰረታዊ ከሆኑት ነጥቦች ዋናኛው የከዋኒ መኖር ነው ። ከዋኒ ስንልም በአንድ የተወሰነ አጋጣሚ አንድን ስነቃል በመሪነት የሚያቀርብ ፡ የሚያሰማ ወይም የሚከውን ግለሰብ ወይም ቡድን ማለታችን ነው ። የለቅሶ ግጥሞችን የሚደረድሩ ግለሰቦችም በት ግርኛ ‘መልቀሳይ (አልቃሽ) ይባላሉ ። በትግርኛ ተናጋሪ ብሄረሰብ አልቃሽ ለመሆን እድሜና ጾታ አይወስነውም ። አዋቂ፣ ወጣት፣ ወይም አዛውንት ፡ ወንድም ሆነ ሴት አልቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ ። አልቃሽ ለመ ሆን የሚገፋፋ ምክንያት እስካላቸው ድረስ ። ሰዎች አልቃሽ የሚሆኑት በተለያየ አነሳሽ ምክንያት ነው ። አብዛኛዎቹ የቅርብ ቤተሰብ ማለት አ ባት ፡ እናት ፡ እህት ፡ ወንድም ፡ ልጅ ፡ ባል ፡ ሚስት ሲሞትባቸውና ሀዘኑ

ጠልቆ ልባቸውን ሲነካው የማይጠፋ ረመጥ ሆኖ በየጊዜው ሲያንገበግባቸው ይቆይና ለቅሶና ቀብር ባገኙ ቁጥር የሞተባቸውን ቤተሰብ በማስታወስ ያለቅሳሉ ። ሀዘኑ እየበረታባቸው ሲሄድም የታመቀውን መሪር ሀዘን ለመግለፅ ይገደዳሉ ። በዚህ ሁኔታ ከጊዜ በኋላ አልቃሽነቱን የለት ተለት ስራቸው አድርገው ይይዙታል ።

አንዳንዶቹም በኑሮአቸው ላይ ከባድ ችግር ሲደርስባቸው ፣ ህልውናቸውን የሚፈታተን መከራ ሲገጥማቸው ፣ ችግራቸውንና ብሶታቸውን ለመግለፅ ይገደዳሉ ። በተለይም "መሬት ላራሹ" ከመታወጁ በፊት በመሬት ክርክር ፣ በዳኞች ፍርድ መዛባት ፣ ገበሬው ከፍተኛ ችግር ይደርስበት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው ። በዚህ ጊዜ የደረሰባቸው ችግር በዳኞችና በባለስልጣኖች ዘንድ ሰሚ ስለሚያጣ በሚያገኙት የለቅሶ አጋጣሚ ብሶታቸውንና ሮሮአቸውን ይተነፍሳሉ ። ከዚያም ለሞተ ቤተሰባቸው ማልቀስ ይቀጥሉና ቀስ በቀስ አልቃሽ ይሆናሉ ። በዚህ መልክ አልቃሽ የሚሆኑ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በተለያዩ የህብረተሰቡ ችግሮች ላይ በማተኮር መግጠም ያዘወትራሉ ።

በዚህ ሁኔታ አልቃሽ የሆኑ በአክሱም አውራጃ ፣ በአክሱም ከተማ ናሪ የሆኑ አንድ ግለሰብ የመሬት ክርክር ስለነበረባቸው ያጠራቀሙትን ሀብት በጉቦ ይጨርሳሉ ። ይኼም ሆኖ ጉዳዩ ስላልተፈጸመላቸው ከቀሩዋቸው ፍየሎች ሁለቱን ሸጠው ተጨማሪ ጉቦ ለመስጠት ወሰኑ ። ባለቤታቸውን እንዳያማክሩ ስለማትፈቅድላቸው እንዳታውቅባቸው የሚሸጡትንና የማይሸጡትን ፍየሎች አስይዘው ልጆቻቸውን ወደ ገበያ ላኩዋቸው ። ከነዚህ ፍየሎች መካከል ባካባቢው በወላድነቷ የታወቀችው ፍየል አንዷ ነበረች ። ገበያ እንደደረሱም የአውራጃው አስተዳደር ፀሐፊ የነበረ ሰው ልጆቹን አስፈራርቶ ፍየሏን ነጥቆ ወሰዳት ። ልጆቹም ሌሎቹን ሳይሸጡ ተመለሱ ። ሰውየውም ነገሩ ሁሉ ሊሳካላቸው ባለመቻሉ እጅግ ተናደዱ ። በሌላ ጊዜ ፍየሏን የወሰደባቸው ሰው አባት ሲሞቱ በቀብሩ ተገኝተው ስለሟቹ ትንሽ ኩተናገሩ (ከደረደሩ) በኋላ ስለደረሰባቸው ችግር እንዲህ ሲሉ ቀጠሉ፣

(1) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| ቀባራየ ሓንሻብ ስምዐና | ቀባሪ አንዴ አድምጠን |
| ክንፀዊ ደሊና ትሽግርና | ችግራችንን ለመናገር ፈለግን |
| ብዳኛታት አክሱም ተቀቢርና | በአክሱም ዳኞች ተቀበርን |
| ደቃቶም ከነዕቢ ንሕና ቆሚልና | ልጆቻቸውንለማሳደግ በቅማልተበላን |
| ንሳቶም ሱፍ ክኸደኑ ንሕና ዓቢቅና | እነሱሱፍ ሲለብሱእኛን እከክወረረን |
| ቅርሺ ሂብናዩም በጊዕ አምፅ | ብር ብንሰጣቸው 'በግ አም |

| | |
|---|---|
| ኡልና | ጡልን |
| በጊዕ ሂብናዮም ጠስሚ ወስኹና | በግ ብንሰጣቸው ቅቤ ‘ጨም ሩልን’ |
| አንስቶም ተዘይተቅቢለነኦም ሕር ሞም ከይረድኡና | ሚስቶቻቸው ካልተቀበሉ እርም ነው ላይረዱን |
| አረ ናይ አቶ ግርማይ ሸጊሩና | ኧረ የአቶ ግርማይ ባሰብን |
| ክርምቲ ኮይኑ ፀጊሙና | ክረምት ሆኖ ቸግሮን |
| ክልተ ጤል አውሪድናየን ንዕዳጋ ሼጥና | ሁለት ፍየሎች ገበያ ወስደን ሸጥን |
| ደቅና ከነዕቢ ሓሲቢና | ልጆቻችንን ለማሳደግ አስበን |
| ክይንዘርእ መስከረም ምድሪ ከቲሮሙና | እንዳንዘራ በመስከረም ጊዜ ዘረፉን |
| እዞም ሰብአይ እዚኦምየ ተዝቅ የሩልና | እኒህ ሰው ቢቀየሩልን |
| መሚዞ ክንከፍሬ መሳፈሪ መኪና | የመሳፈሪያስሙኒስሙኒእንከፍላለን |
| መንግስቲ ደሞዝ እናኸፈለ ንስ ኻትኩም ወስኹና | ጨምሩን ይሉናል ደመወዝ እየተከፈላቸው |
| ወይ ናይ መንግስቲ ይቅረ ክንቅ ልቦም ባዕልትና | ወይ ደመወዙ ይቅር እኛ እን ቀልባቸው |
| ክልቴና አይንባኸንየ ንተሐላሎ ኢና | ሁለታችንም አንባክንእንንቃባቸው |
| እረ ናይ አውራጃ ፍርድቤትየ ፀጊሙና | እረ የአውራጃ ፍርድ ቤት ቸገረን |
| ብየማን ብጸጋም ዓበይቲ ዘናጋሪር ዘይተኸፍተ ሽክና | ቡቀኝና በግራ ያሉት ያልተከ ፈተ ሽክና ትላልቅ ጋን |
| እዚአቶም እናሃለውየ እንታይ ክን ከውን ኢና | እነዚህ እያሉ ምን እና ደርጋለን |
| ክረምቲ እንተወጺኡየ ዓተባሕሪ ሼጥና ክንዛነኢና | ካለፈ ክረምቱ ባቄላ ሸጠን እንዝናናለን |
| ኮነሬል በላይ ግዳ ብዘይ ህጊ አሲሩ ይሰደና | ኮሎኔል በላይ ግን አለህግ ያስረናል |

ብለው ለመጀመሪያ ጊዜ በማልቀስ ከዚያ በኋላ በየአጋጣሚው እየተገኙ በመግጠም አልቃሽ ሆኑ ።

ሌሎች ደግሞ አልቃሽ የመሆን ፍላጎት ያድርባቸዋል ። ከዚህም ፍላጎት የተነሳ፣የሚያውቋቸውን ታዋቂ አልቃሾች እንዲያስተምሩ ዋቸው ይጠይቃሉ ። አልቃሾቹም ቡመጀመሪያ ቀደም ብለው የገጠ ሙዋቸውን ግጥሞች በማስጠናት ትምህርቱን ይጀምራሉ ። ተማሪዎ

ቹም ግጥሞቹን በቃላቸው ደግመው ደጋግመው ያጠናሉ ። በዚህም ወቅት የቃላት አመራረጥ ፣ የዓረፍተነገር አሰካክ ፣ የቤት አመታትን ፣ የሀሳብ አቀነባበርን ወዘተ- በሚገባ ይገነዘባሉ ። ከዚያም ራሳቸው መግ ጠም ይጀምራሉ ። ወዳጅ ዘመድ ሲሞትባቸው ግጥም መደርደር ይቀ ጥላሉና ቀስበቀስ ችሎታቸውን እያዳበሩ በህብረተሰቡም ዘንድ እየታ ወቁ ይሄዳሉ ። በዚህ ሁኔታ በፍላጎታቸው አልቃሽ የሆኑ በአድዋ አው ራጃ ኗሪ የሆኑ አቶ አባይ መዓሾ የተባሉ ግለሰብ በአንድ አጋጣሚ እን ዲህ ብለው አልቅሰው ነበር ።

| | |
|---|---|
| (2) ሓንቲ እንኤትኒ ሓንቲ ዘረባ<br>ገረስላስ ሰዓረ ዝመሃሩኒ ንእለትየ ዝቅልባ | አንድ ነገር አለኝ የምለው<br>ገ/ስላሴ ሰዓረ ያስተማሩኝን<br>ባንዴ ነው የማጠናው (የም<br>ቀልበው) |
| አይንኤኹንዶ ወኪሎም ቀዲደ ዝል<br>ግባ ንዘረባ | አለሁ ምትካቸው ነገርን ቀድጄ<br>የምሰፋው |

ይህ ግጥም አቶ አባይ መዓሾ ‘ተማሪ’ በነበሩበት ወቅት አቶ ገ/ ስላሴ ሰዓረ የተባሉ ታዋቂ አልቃሽ ያስተማሯቸውን በሚገባ እንደያ ዙና አሁን አቶ ገ/ስላሴ ሲያረጁ እሳቸውን ለመተካት የቻሉ መሆናቸ ውን ያስገነዝበናል ።

እነዚህ በተለያዩ ምክንያቶች አልቃሽ የሚሆኑት ሰዎች የትምህ ርት (የቤተክህነት) ሁኔታ ፣ የቋንቋ ችሎታ ፣ ወዘተ- የተለያየ ስለሆነ የመግጠም ችሎታቸውም የዚያኑ ያህል የተለያየ ነው ። ኅብረተሰቡም በአልቃሾቹ ላይ ያለው አመለካከት ብዙውን ጊዜ በችሎታቸው ላይ የተመረኮዘ ይሆናል ። ሰዎች በሚገናኙባቸው እንደ ጠላ ቤት ፣ ማህበር ፣ እድር ወዘተ- የመሳሰሉ ቦታዎች ፣ አልቃሾች ሲገኙ ሰዎቹ ችሎታቸውን ይፈትኗቸዋል ። አንዳንድ አልቃሾችም የፈጠራ ችሎታቸው ከፍተኛ ይሆንና ስለአንዳንድ ሁኔታዎች ወድያውኑ ይገጥማሉ ። በዚህም በአካ ባቢያቸው እንደ ቀልደኛ ይቆጠራሉ ። ለአብነት ያህል በአድዋ ከተማ የምትኖር አንዲት ጠላ ሻጭ ፣ ቡና አጥታ ስለተቸገረች ፣ አንድ ብርሃኔ ተስፋዬ የተባሉ ታዋቂ አልቃሽ ጠላ ለመጠጣት ወደ ቤቷ ሲገቡ ፣የቡና ሱስ እንዳስቸገራትና ቡና እንዳላገኘች ገልጻ ቡናን በሚመለከት እንዲ ገጥሙላት ትጠይቃቸዋለች ። እሳቸውም ።

| | |
|---|---|
| (3) ከመዓልኪ ጀበና ጀበና<br>ታሪክ አለኒ ናትኪ ዜና<br>እንትርፊ ፈታዊ ዘይብልኪ ንና | እንዴት ዋልሽ ጀበና ጀበና<br>ታሪክ አለኝ ስላንቺ ዜና<br>ወዳጅ እንጂ የለሽም ባዳ<br>(ጠላት) |

| | |
|---|---|
| ጅማ አባጅፋር ገዛኺ ለምለም ማና | ጅማ አባ ጅፋር አገርሽ ለም ለም መና |
| አዲስ አበባ ገዛኺ ለምለም ማና | አዲስ አበባ አገርሽ ለምለም መና |
| እስኺ ትትፍጠሪ ኅበዝ ዝነበረ ስኢኑ ጥዕና | አንቺ ስትፈጠሪ ኅበዝ የነበረ አጣ ጤና |
| ቆንጆ ዝንበረትበአኺ ስኢና ጥዕና | ቆንጆዋም ባንቺ አጣች ጤና |
| በዓል ሐዳር ገበርክዬ ምናምና | ባለትዳርን አደረግሽው ሱሰኛ |
| በዓል ድንኳን ገበርክዩ ዑና | ባለሱቅን አደረግሽው ያና |
| ወልፈኛ ዝነበረት ብአኺ ተን ቁሕ ዓይና | ሱሰኛዋ ባንቺ ይበራል አይኗ |
| በዓል ወልፊ ይደልየኪ ወሪዱ ካብ መኪና | ሱሰኛውም ይፈልግሻል ወርዶ ከመኪና |
| ብገርሂ ዘይትርኸብ ተለሚና | በቀላሉ አትገኝም ተለምና |
| ክንዲ ኮበርታ ሐሙኽሽቲ ክዳና | በብርድልብስ ፈንታ አመድ ልብሷ |
| ቁርሲ እንትተምፅእ እምሪሐ ዕጣና | ቡና ቁርስ ስታስመጣ እጣኗን አስከትላ |
| ሐናኽ ወይዘሮ ትመስል ንቁል ቁሉ ደኒና | ዓይናፋር ወይዘሮ ትመስላለች አጎንብሳ |
| ጭራ ብዕራይ ጌራ ቅርንብ ዓይና | የበሬ ጭራ አድርጋ ቅንድቧ |
| ጻዕዳ ፍንጃል ጌራ ደርጊ ስና | ነጭ ስኒ አድርጋ ጥርሶችዋ |
| ተፈታዊት ኮይና ከም መዓር ፅዴና | እንደ ጣዝማ ማር ተወዳጅ ሆና |
| ከም ሽይጣን ተኺላ ሐደ እዝና | እንደ ሰይጣን አንድ ጆሮዋን ተክላ |
| ጀበና አንቲምናምና | ከንቱ ነሽ ጀበና ጀበና |

በማለት በጊዜው ለተጠየቁት ጉዳይ ወድያውኑ በመግጠም በጠላ ቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሁሉ አሳቁዋቸው ። በዚሁም ሰውየው እንዲህ የመሰለ የመግጠም ችሎታ ስላላቸው ከአልቃሽነታቸው በተጨማሪ እንደ ቀልደኛ መታየት ጀመሩ ።

አልቃሾች በኅብረተሰቡ ዘንድ የተከበሩ ናቸው ። የፈለጉትን ነገር በብዙ መንገድ መግለጽ ስለሚችሉ ፣ የሰሙትንና ያዩትን ስለሚያጋ ልጡ በባለስልጣኖች ፊት ሳይቀር ይፈራሉ ። በመቀሌ አካባቢ ታዋቂ የነበሩት ብላታ ሀብተስላሴ የተባሉ አልቃሽ ወደ ቤተ መንግስት ለግ ብዣ ተጠርተው ይሄዳሉ ።

አሳላፊውም ጠጅ ይቀዳላቸዋል ። ድገማቸውም ሲባልም ደግሚያቸዋ ለሁ አለ ተሳስቶ ። በዚህ ተበሳጭተው 'ስሙ ማነው' ብለው ጠየቁ 'ታመነ' ተባሉ ፤ አገሩም አፋር መሆኑ ተነገራቸው ።

(4) ታመነ ታመነ ታመመ — ታመነ ታመነ ታመመ
አብ ክብዲ እንኡ ተሎ ልተሐመ — በናቱ ሆድ ውስጥ እያለ የታመመ
እኖታትካ እሊ ዒሳ እሊ ፋጢመ — እናቶችህ እነ ዒሳ እነ ፋጢማ
አቦታትካ እሊ ዓብዱ አርሒመ — አባቶችህ እንዓብዱ አርሒመ
ወዬ ክበልዕ ክሰቲ ተዓዲመ — ልበላ ልጠጣ ተጋብዤ
ሃም በቅሊ ነጋዳይ ተሓልኪም — እንደ ነጋዴ በቅሎ ተቀይጄ
ሃም በቅሊ ዓቀይታይ ተለጕመ — እንደ ወታደር በቅሎ ተለጉሜ
ደጊምካዶ ተበሉዎስ እወ ደጊመ — ደገምከው ወይ ቢሉት 'አዎ ሰጠሁት ደግሜ'
አባ ጋብርከ ኣይ ሃብካ ዕድመ — አቦ አይሰጥህ እድሜ

ብለው ሲሰድቡት መኳንንቱም አሳላፊውን ጠርተው ሄደህ ይቅርታ ጠይቅና ቅዳላቸው አሉት ። እሱም ሄዶ ይቅርታ ጠይቆ ቀዳላቸው ። እሳ ቸውም እንደገና ፤

(5) ታመነ ታመነ — ታመነ ታመነ
ለይሕመደሎ ልተሾመ — የማይታማ አለ ወይ የተሾመ

በማለት ቅሬታቸውን በመተው መልሰው አጽናኑት ።

ከላይ ሰዎች እንዴት አልቃሽ እንደሚሆኑና የፈጠራ ችሎታቸውም ምን ያህል እንደሆነ ለመግለጽ ተሞክሯል ። እነዚህ አልቃሾች ባላቸው የፈጠራ ችሎታ ተጠቅመው በለቅሶ አጋጣሚ የሚያስተላልፏቸው መል እክቶች ምን እንደሚመስሉ ቀጥለን እንመለከታለን ።

### 1.2.1 በለቅሶ አጋጣሚው የሚተላለፉ መልእክቶች

በአፍሪካ ስነቃል ጥናት ያካሄዱት ምሁር ሩዝ ፊነጋን (1970:272) "ባል ሰለጠነው ኅብረተሰብ ውስጥ ቃላዊ ግጥሞች የጋዜጣን ቦታ ይይዛሉ" በማ ለት ቃላዊ ግጥሞች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ ገልጸዋል ። የጋዜጦች አገልግሎት ለማንኛችንም ግልጽ ነው ። ቃላዊ ግጥሞችም የጽሁፍ ጥበብ ሳይስፋፋ እንደአሁኑ የጋዜጦች ህትመት ሳይ በራከት የጋዜጦችን ቦታ ይዘው የኅብረተሰቡን ዕለታዊ ኑሮ የሚያንጸ ባርቁ ፣ ድክመቶችን የሚጠቁሙ ፣ የሚተቹና የሚያርሙ ህዝቡን በማ ስተማር ፣ በመቀስቀስና በማስተባበር በኩል ከፍተኛ ሚና የተጫወቱና ዛሬም በአንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያሉ ናቸው ። እንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት ያበረከቱት ከነበሩ ቃላዊ ግጥሞች የትግርኛ የለቅሶ ግጥሞች ይገኛሉ ።

በትግርኛ ተናጋሪ ብሄረሰብ የለቅሶ አጋጣሚው ሞት ይሁን እንጂ አልቃሾች ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ሟችን በሚመለከት ከሚደረድሩዋቸው ግጥሞች በተጨማሪ የኅብረተሰቡን ወቅታዊ ሁኔታዎችን ያንጸባርቃሉ ፣ ያለፈውን ታሪኩንና ባህሉን በሚመለከት ይናገራሉ ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚከሰቱትን አስተዳደራዊ ችግሮችን ፤ የፍትህ መዛባትን ፣ የዳኝነት መጓደልን ፣ የኢኮኖሚ ችግሮችን ፣ የፖለቲካና ወታደራዊ ግንኙነቶችንና ግጭቶችን ፣ ተንኮልን ፣ ክፋትን ወዘተ ፣ በሚመለከት ግጥሞችን በመደርደር ከፍተኛ የቅስቀሳና የፕሮፖጋንዳ ተግባር ያከናውናሉ ። በዚህ አይነት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ጉዳዮችን በሚመለከት የተደረደሩ የለቅሶ ግጥሞች በርካታ ናቸው ። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹን በአራት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በማጠቃለል ለማቅረብ እንሞክራለን ።

### 1.2.1 አስተዳደራዊ ችግሮችን የሚመለከቱ

ቅድመ አብዮት የኢትዮጵያ ገበሬዎች በብዝበዛና በጭቆና ቀንበር ወድቀው ሲማቅቁ ነበር ። ዘመኑም ዳኝነት የጎደለበት ፣ ፍትህ የተዛባበት ፣ ጉቦኝነት የነገሰበት ዘመን ነበር ። የትግርኛ ተናጋሪ ብሄረሰብም የፊውዳሉ ስርዓት ያደርስበት የነበረውን ግፍና ጭቆና በመቃወም ችግሩንና ብሶቱን ከሚያሰማባቸው መድረኮች አንዱ የለቅሶ አጋጣሚ ነበር ። አልቃሾች ይህንን አጋጣሚ ሲያገኙ ስርዓቱንና የስርዓቱ ውጤቶች የሆኑትን አስከፊ ገጽታዎች በመቃወም ፣ ህዝቡን በማነቃቃት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ። ይህንን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ከተለቀሱት መካከል ጥቂቱን ቀጥለን እንመለከታለን ።

| | | |
|---|---|---|
| (6) | ብባርላማ ዓለም ተናወፁ | በፓርላማ ዓለም ተናወጠ |
| | መሸላና ቦቁሉ ነቂፁ | ማሽላችን በቅሎ ደረቀ |
| | ዳጉሻና ቦቁሉ ነቂፁ | ዳጉሳችን በቅሎ ደረቀ |
| | ቶም ሰብ ስልጣን ባዕሎም ከይ<br>መርፁ | ባለስልጣኖቹ ራሳቸው እንዳይ<br>መርጡ |
| | ዘይንፈልጦ ሕጊ ሒዞሙ<br>ጳና መጹ | የማናውቀውን ህግ ይዘውልን<br>መጡ |
| | ዝበዝሐ ክደኽዩ ክልተ<br>ክምረፁ | ብዙዎቹ ሊደኸዩ ሁለት<br>ሊመረጡ |
| | ነዓይ ነዓይ ህዝብ ተቃፂ | ህዝቡ ተሻማ ለኔ ለኔ ብሎ |
| | ገንዘቦም ተረፈ ተረሚፁ | ገንዘባችን ቀረ ባክኖ |
| | እንታይዶ ይዓብሱ እዩም ተተ<br>መርፁ | ምን ይፈይዳሉ ቢመረጡ |

| | |
|---|---|
| አብ ባር አትዮም ቢራ ተጎፀጎፁ | ቡና ቤት ገብተው ቢራ ቢጠጡ |
| አብ ሆቴል አትዮም ጮማ እን ተቆረፁ | ሆቴል ገብተው ጮማ ቢቆርጡ |
| በቅሊ ዘይነበሮም ብመኪና መፁ | በቅሎ እንኳን ያልነበራቸው በመኪና መጡ |
| አድጊ ዘይነበሮም ብመኪና መፁ | አህያ እንኳን ያልነበራቸው በመ ኪና መጡ |
| ዘይዕዳና ሒዘሙልና መጹ | የማናውቀው ዕዳ ይዘውልን መጡ |
| ብቦለቲክ ክንዳይ ተበለፁ ። | በፖለቲካ ስም ብዙ አላገጡ ። |

ከላይ የተጠቀሰውን ግጥም የደረደሩት አቶ ገብረሚካኤል ዕሩይ የሚባሉ በአክሱም አውራጃ የሚኖሩ አልቃሽ ሲሆኑ የፊውዳሉ ስርአት በተለይም በፓርላማ ተመራጭነት ስም ህዝቡን ሲበዘብዙና ሲያስቃዩ እንደነበሩ በአንድ የቀብር ስነስርአት ወቅት ያለቀሱት ነው ። ይህም ህዝቡ በለቅሶ አጋጣሚ ስርአቱን ይቃወም እንደነበር ያስረዳል ። ከዚሁም ሌላ በአክሱም አውራጃ የነበረ አንድ ገበሬ ደግሞ የመሬት ጉዳይ ስለነ በረው እስከ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ተከራከረ። ያፈራውን ሃብትና ንብ ረት እስኪሟጠጥ ድረስ ተሟገተ ። በመጨረሻም ፍርዱ ተዛብቶ ተረታ ። በዚህም ጊዜ ተስፋ ቆርጦ ሲንከራተት ድንገት ቀብር አገኘና ፤

(7) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| ነገር ኄራትኒ ወሰድኩዋ ናብ ወኪል | ነገር ነበረችኝ ወሰድኳት ወደ ወኪል |
| አብአ እንድያ ንቅደም እት ሕክል | እዛም ነው መጀመሪያ የምት ሰናከል |
| ነገረይማ ወሰድኩዋ ናብ ጭቃ | ነገሬንማ ወሰድኳት ወደ ጭቃ |
| አብአ አበየትኒ ተሐኒቃ | እዛም ቀረች ታንቃ |
| ነገረ ይማ ወሰድኩዋ ናብ አጥቢያ | ነገሬማ ወሰድኳት ወደ አጥቢያ |
| አብአ አበየትኒ ተጠውያ | እዛም ቀረች ተቀልብሳ |
| ነገረይማ ወሰድኩዋ ናብ ወረዳ | ነገሬንማ ወሰድኳት ወረዳ |
| አብአ አበየትኒ ተዋሪዳ | እዛም ቀረች ተዋርዳ |
| ነገረማይ ወሰድኩዋ ናብ አውራጃ | ነገሬንማ ወሰድኳት አውራጃ |
| አብ ፅምዲ ብዕራይ ኄርካስ ናብ ሐደ ቃንጃ | ባለ ጥንድ በሬ ነበርኩ ሆኜ ቀረሁ ባለ ቀንጃ |
| ፀሐፎ ለብዘበን ዳኛታት ለብ ዘበን ብኡነት ፍረዱ | ዳኞችና ፀሃፊዎች ለእውነት ይሁን ፍርዳችሁ |
| ብገንዘብ ድኻ ከብድኹም ተቀዲዱ | በድሃ ገንዘብ ነው የሞላው ሆዳችሁ |

| | |
|---|---|
| ምኲት ኮይንኩም ዲኹም ክት ሕረዱ | ልትታረዱ ነው ወይ ሙክት ሆናችሁ |
| ብዕራይ ኮይንኩም ዲኹም ክት ፅመዱ | ልትጠመዱ ነው ወይ በሬ ሆናችሁ |
| ከም አብዑር ሕዳር ማእገርኩም ሰዊዱ | እንደ ኀዳር በሬ ዳበረ አንገ ታችሁ |
| አቦይዝጊ ክጥየቅኩምዩ ንጴጥሮስ አውሪዱ | እግዚአብሔርም ጴጥሮስን ይል ካል ሊጠይቃችሁ |
| ሰይጣን ክገብረኩምዩ ቦኽሪ ወዱ | የሰይጣን በኩር ልጅ ትሆናላችሁ |

ብሎ የደረሰበትን መጉላላትና መከራ ተናግሮ ወደ ስደት ሄደ ።

እንደዚሁም አንዲት ወ/ሮ ደበስ የሚባሉ ሴት የመሬት ክርክር ስለነበራቸው ብዙ ዓመታት ከተከራከሩ በኋላ ፍርዱ የሚሰጥበት ወቅት እየተቃረበ ሲመጣ ባላጋራቸው ጉቦ ሰጥቶ ፋይላቸውን እንዲደበቅ ያደ ርጋል ። ፋይላቸው የጠፋ መሆኑና ተፈልጎ ሊገኝ አለመቻሉን በፍርድ ቤቱ ተነገራቸው ። ሆኖም የተደበቀ መሆኑን ሰሙና በወቅቱ ባገኙት የለቅሶ አጋጣሚ እንዲህ ብለው ያለቅሳሉ ፤

(8) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| ሐደ-ሰብአይ ጨለቆት ልዓዱ | አንደኛው ሰው ጨለቆት አገሩ |
| ሐዲኡ እንዳመኾኒ ልዓዱ | አንደኛው መኾኒ አገሩ |
| ሐዲኡ ዘፍጣጥ ከብዱ | ሌላኛውም ቦርጫም ሆዱ |
| ብደበላ ጤሊ ልማለዱ | በሰባ ሙክት የሚማለዱ |
| ብንቅዓ ጣፍ ወረቅት ልቀዱ | በቁና ጤፍ ወረቀት የሚቀዱ |
| ጃንሆይማ እዙኹለይ ለይፈል ጥዎ ጉዱ | ጃንሆይ ግን ይህን ሁላ አያው ቁትም ጉዱ |
| ዝብኢ ሰዲዶሙሉ በብዓዱ | ጅብ ለቀቁበት በያገሩ |

## 1.2.2 ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን የሚመለከት

ኢትዮጵያ ከውጭ ወራሪ ሀይሎች ጋር በተደጋጋሚ ጦርነቶችን አካሂዳለች ። በጦርነቱም በድል አድራጊነት ድንበሯንና ነፃነቷን አስከ ብራለች ። ህዝቡም የተገኘውን ድል በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጿል ። ሃገራችንን ለመውረር ከመጡት የውጭ ወራሪ ሃይሎች ኢጣሊያ አንዷ ስትሆን የፋሺስት ኢጣልያ ጦርም በተደጋጋሚ ድል እየተመታ መመለሱ የሚታወቅ ነው ። በዚህም ወቅት ኅብረተሰቡ ድሉን በተለያየ መልክ

ሲገልጽ ቆይቷል ። አልቃሾችም በለቅሶ አጋጣሚ ድሉን ያበስሩ ነበር ። ከዚህም መካከል ፣

(9) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| ስምዑንዶ ፋሺስት ጥልያን ዝገበረ | ስሙኝማ ፋሺስቲ ኢጣልያ ያደረገው |
| ስምዑኒማ ኢጦብያ ፅን ኢልኩም ዝወረ | ስሙኝማ ኢትዮጵያ በጥሞናወሬው |
| አስመራ መንደፈራዶ ናቱ ዘይ ነበረ | አስመራ መንደፈራ በሱ ስር አል ነበረም ወይ |
| መቀለ ሸዋደ ናቱ ዘይነበረ | መቀሌ ሸዋ በሱ ስር አልነበረም ወይ |
| ስምዑኒማ ፅን ኢልኩም ዝወረ | በጥሞና ስሙኝማ ይህን ወሬ |
| ኢያ ጥልያን ክነገረሉ ታሪክ ሂወቱ | የኢጣልያ ህይወት ታሪኩን ላውራለት |
| ላቢስ ዕርፋ ወረቅት ግራቱ | እርፋ እርሳስ ነው ማሳው ወረቀት |
| ሰልዲ ጉርዱ ፈረንካ እቶቱ | ሳንቲም ግርዱ ብር ምርቱ |
| እያ ጥልያን ክንገረሎም ናቶም | የኢጣልያኖች ላውራላቸው ማን ነታቸው |
| ሰማይ ሰማይ ትብርር ኔራቶም | ሰማይ ሰማይ የሚበር ነበራቸው |
| ባይታ ባይታ ትሽክርከር ነይራቶም | መሬት መሬት የሚሽከረከር ነበራቸው |
| ርኢኹምዶ ሎሚ ዓለም ጠሊማቶም | አያችሁ ወይ ዛሬ ዓለም ከዳቻቸው |

በማለት ኢጣሊያኖች የደረሰባቸውን ሽንፈት ገልጸዋል ። ኢጣልያን ተሸንፎ እንደወጣም አንዲት ሴት ፣

(10)

| | |
|---|---|
| እዚኦም ድዮም ዞም ፀዓዱ ዞም ዝሐመሙ | በሽተኞቹ ፈረንጆች እነዚህ ናቸው ? |
| አዒንቶም ዝመስል ንደማሙ | ድመት የሚመስሉ ዓይኖቻቸው |
| አፋቶም ዝመስል ዕንጣጢዕ ዝቆሓሙ | ተልባ የቃሙ የሚመስል አፋቸው |
| አራእሶም ዝመስል ሻሻ ዝጠምጠሙ | ሻሽ የጠመጠሙ ይመስላል ራሳቸው |
| እምበአር እዚኦም ድዮም ደቂ ቱርክያ | እኒህ ናቸው ለካ የቱርክ ዘሮች |

| | |
|---|---|
| ደው ኢሉም ዘይትኩሱ ትርፌ ጉያ | ቁመው የማይዋጉ ፈርጣጮች |
| ደው ኢሎም ዝቁረፁ ከም ሙግያ | ዝምብለው የሚጨፈጨፉ እንደ ሙጃ |
| ዘፍ ኢሎም ተረፉ ከም ፋንድያ | ተዘርግፈው ቀሩ እንደ ፋንድያ |

ብላ በመግጠም በኢጣልያ ላይ የደረሰውን ውድቀት ባገኘችው አጋጣሚ ገልጻለች ። ከዚህ ሌላ አጋጣሚን ተጠቅመው በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታዎች ይገልጻሉ ። መሪዎቻቸውን ለጦርነት ያበረታታሉ ያነቃቃሉ ። አፄ ዮሐንስ ልጃቸው ልጅ አርአያ እንደሞቱ ረዘም ላለ ጊዜ ሀዘን ላይ ተቀምጠው ስለነበር ወ/ሮ ጥሩ የሚባሉ አልቃሽ ፥

| | |
|---|---|
| (11) ጃንሆይ እምብዛም አይትንደዱ | ጃንሆይ እምብዛም አይናደዱ |
| ንጉሰለዶ ይሐዝን ናይ ከብዱ | ንጉስ ያዝናል እንዴ ከሆዱ |
| ሰራዊትኩም ሒዝኩም ጎጃም ኪዱ | ሰራዊትዎን ይዘው ጎጃም ይሂዱ |
| አዞም ጎጃም ልበረኻ ከይኸዱ | ጎጃሞች በረሃ እንዳይሄዱ |
| ሰራዊትኩም ሒዝኩም ሸዋ ኪዱ | ሰራዊትዎን ይዘው ሸዋ ይሂዱ |
| እዞም ሸዋ ልበረኻ ከይኸዱ | ሸዋዎቹ ፥ በረሃ እንዳይሄዱ |
| ሰራዊትኩም ሒዝኩም መተማ ኪዱ | ሰራዊትዎን ይዘው መተማ ይሂዱ |
| እዞም ጸላእቲ ኢዶም ከይሰዱ | ጠላቶችዎ እጃቸውን እንዳይሰዱ |
| ክርስቶስከ ወድዶ ወሊዱ | ክርስቶስም (ፈጣሪ) ወልዶ ነበር ልጁ |
| ንጉሳችን አንተ ትበቃለህ አንዱ | ንጉሳችን አንተ ትበቃለህ አንዱ |

ብለው የማበረታቻ ግጥም ደረደሩላቸው ። በሀዘን ምክንያት ረስተውት የነበረውን የአካባቢያቸውን ውጥረት በማስታወስ ከሀዘናቸው ተነስተው እንዲዘጋጁ አደረጉዋቸው ። በተጨማሪም አፄ ተክለጊዮርጊስ ከአፄ ዮሐንስ ጋር ከመዋጋታቸው በፊት የሰራዊታቸውን ብዛት ለማሳየት በበርካታ አህዮች ጤፍ አስጭነው ወደ አፄ ዮሐንስ በላኩባቸው ጊዜ አንዲት አልቃሽ አፄ ዮሐንስን ለማበረታታት እንዲህ ብላ ነበር ፣

| | |
|---|---|
| (12) ትብልያለኻ በሰራይት ይበዝሑኒ | ትላለህ አሉ በሰራዊት ብዛት ይበልጡኛል |
| ትብልያለኻ ብሮማይ ይበልጹኒ | ትላለህ አሉ በመሳሪያ ይበልጡኛል |
| አብኒወልድኒ መንፈስ ቅዱስኒ | አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ |
| ጐልያድማ መጸ ንዳዊት ከግኒ | ጐልያድማ መጣ ዳዊትን ለመግደል |

| | |
|---|---|
| ዳዊት ዘቀተሎ በአሃተ እምኒ | ዳዊት ግን ገደለው በአንዲት ድንጋይ |
| ሎሚውኒ ከምአ ደአ ትመስለኒ | ዛሬም ታድያ እንደዛው ይመ ስለኛል |
| ሃየ እንቁጣጣሽ ከይትርስዑኒ | አደራ እንቁጣጣሽ እንዳይረሱኝ |

ከወራሪ ጠላት ጋር ከሚደረጉት ጦርነቶች ሸሽተው የሚመለሱ ትልቅ ውርደት ይደርስባቸዋል ። ኅብረተሰቡም የሚሰጣቸው ግምት ዝቅተኛ ይሆናል ። አጼ ዮሐንስ መተማ በጦርነት እንደሞቱ ፣ እሳቸው ጋር ከነበሩ ተከታዮቻቸው መካከል ሊቀ መኳስ የተባሉ ሰው ሸሽተው አገራቸው እንደገቡ አንዲት የተንቤን አልቃሽ እንዲህ ብላ ገጥማለች ፣

| | |
|---|---|
| (13) እዞም እንደርታ እንታይ ጉዶም | እነዚህ እንደርቶች ምን ጉድ ናቸው |
| ወርቂ ኮረቻ አስሪሮም ከማኦም | ወርቅ ኮረቻ ተፈናጥጠው እን ደሳቸው |
| ወርቂ አልቦያ አእትዮም ከማኦም | ወርቅ አልቦ አጥልቀው እን ደሳቸው |
| ግምጃ ስረያ አዕጢቆም ከማኦም | ግምጃ ሱሪ ታጥቀው እንደሳቸው |
| ሙሉቀ ቢሎም አተው ዓድየኦም | ሸሽተው ገቡ ወደ አገራቸው |

እንደርቶችም ይህንን ስድብ ሰሙና ምንም እንኳን እሳቸው (ሊቀ መኳስ) ሸሽተው ቢገቡ በአንድ ሰው ብቻ አገሩ በሙሉ መሰደብ እንደ ሌለበትና ሌሎች ጀግኖች በጦር ሜዳ እንደተፋለሙ በመግለጽ የሚከተ ለውን መልስ ሰጡ ፣

| | |
|---|---|
| (14) ሹመትን መልክዕን ጌረን ከይ ጸርፈኦም | ሹመትና መልክ አድርገው እን ዳይሰደቡዋቸው |
| ዕልቢት ወዲዶ ርኢኹን አትዮም | ዕልቢት ወንዱ ገቡ ወይ አያችሁ |
| እል ሃይሉ ስጉዳዶ ርኢኹን አትዮም | እነ ሃይሉ ስጉዳ ገቡ ወይ አያችሁ |
| እል ሓንታ ገራይራምዶ ርኢኹን አትዮም | እነ ሓንታ ገራይራም ገቡ ወይ አያችሁ |
| እንዳርታስ ቃልርዮም ብሙልኦም | እንደርቶችማ በሙሉ ቀሩላችሁ |

በወጀራት አካባቢ እነ ተኽለ ጋሪማ የተባሉ የታወቁ ሰዎች ነበሩ ። ሰባት ሆነው በበርሃ ሲሄዱ ፣ ከሩቅ የኢጣሊያ ሰራዊት ሲመጣ አዩና ሶስቱ እንሽሽ ሲሉ ፣ አራቱ አንሸሽም ብለው በነበሩበት መሽገው ከጠላት ጋር ገጥመው በጀግንነት ሞቱ ። ሶስቱ ግን ሸሽተው አገራቸው ገቡ ። በዚህ ወቅት ለሞቱት ሰዎች ሁለተኛ ቀብር ተዘጋጅቶላቸው ነበርና በዚ ያን አጋጣሚ አንድ አልቃሽ እንዲህ ብለው አለቀሱ ፣

(15) ወየ ወየ ወየ ወዬ

ልገለቡስባ ዓዳቶም አትያቶም የሸሹማ ገቡ አገራቸው
ቅንይ ቢሎም ክወልዱ ወዳቶም ሰነባብተው ሊወልዱ ልጃቸው
ክሻዑለ ክመልኡ ሐጀቶም እስከዛውም ያደራጃሉ ጎጆዋቸው

በሃገራችን የተደረጉት ጦርነቶች ከውጭ ወራሪ ሃይሎች ጋር ብቻ ሳይሆን ህዝቡን በዘር በጎሳና በክልል እየለያዩ እርስ በርሱ እንዲጋጭ ከሚያደርጉ ጥቂት መሳፍንትና ባላባቶች ጋርም ነበር ። በዚህም ወቅት በየወገኑ የነበሩ አልቃሾች ወገናቸውን በመደገፍ የጠላቶቻቸውን ወገን በማጥላላት በየአጋጣሚው ይገጥሙ ነበር ። ቀደም ብሎ እንደተገለጸውም የጦርነቱን ሁኔታ (ዜና) ያቀርቡ ነበር ።

የአድዋ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ገ/ስላሴ የአጋሜውን ገዥ ራስ ስብሐትን በወጉ ጊዜ የእንደርታው ራስ ስዩም ይህንን ሰምተው ይመ ጡና ከደጃዝማች ገ/ስላሴ ጋር ይዋጋሉ ። በወቅቱም ደጃዝማች ገ/ስላሴ ይሸሻሉ ። በዚህ ወቅት እንደርቶች አሸነፍን እያሉ ደስታቸውን ይገ ልጹ ስለነበር ይህንን ያየች አንዲት የአድዋ አልቃሽ ፡

(16) ወየ ወየ ወየ ወዬ

ወዬም እንደርታ ወዬም አዋዑር እኒህ እንደርታ እኒህ በሬዎች
ወዬም ገርዓልታ ወዬም አዋዑር እኒህ ገርዓልታ እኒህ በሬዎች
ወዬም ስለዋ ወዬም አዋዑር እኒህ ስለዋ እኒህ በሬዎች
መሬት መሲዖ እንተበለ ድሕር ጊዜው መሽቶ ዘወር ቢሉላችሁ
መሲሉ ዎምዶ ዝኾነ ስዑር የተሸነፈ መሰላቸው ወይ

ብላ አልተሸነፍንም በማለት ስትገልጽ ነገሩ እንደርታ ይሰማና አንዲት የእንደርታ አልቃሽ እንዲህ ስትል በአማርኛ መልስ ሰጠች ፡

(17)
አንቺ አልቃሽ አንቺ ወስላታ
ተረታ እንጂ ምነው አልተረታ
ደሙ እየታፈሰ በገበታ
በጨለማ ሄደ እየተንገላታ

## 1.2.3 ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚመለከቱ

በኤርትራና በትግራይ ክፍላተ ሃገር በአየር መዛባት ፣ በአምበጣ መንጋ መነሳት ፣ ወዘተ በተደጋጋሚ የድርቅና የረሃብ ችግር ተከስቷል ። በዚሁም አልቃሾች የሁኔታውን አሳሳቢነትና አደገኝነት ይገልጹ ነበር ። የእህል እጥረት ከአባት፣ ከእናት፣ ከወንድም፣ ከእህት ወዘተ ሞት የበለጠ የከፋ እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት ገልጸዋል ። በአጠቃላይ ሁኔታውን በተ ለያዩ መልኮች አቅርበውታል ።

በአካባቢው በአንድ ወቅት ደርሶ የነበረውን ድርቅ አንድ አልቃሽ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል ።

(18) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| አቦኻ ተሞተ ቁሩብ ሐዘን | አባትህ ቢሞት ሀዘኑ ትንሽ ነው |
| እኖኻ ተሞተት ቁሩብ ሐዘን | እናት ብትሞት ሀዘኑ ትንሽ ነው |
| ወድነኻ ተሞተ ቁሩብ ሐዘን | የናትህ ልጅ ቢሞት ሀዘኑ ትንሽ ነው |
| ውላድካ ተሞተ ቁሩብ ሐዘን | የወለድከው ቢሞት ሀዘኑ ትንሽ ነው |
| እኽልን ማይን ጨካን አይሐዘን | እህልና ውሃ ግን ጨካኝ አይ ያዛቸው |

በትግራይ ክ/ሀገር በ1951 ዓ/ም በደረሰው የድርቅ ችግር ደግሞ አንድ አልቃሽ እንዲህ ብሎ ነበር ፤

| | |
|---|---|
| (19) ወየ ወየ ወየ | ወዬ ወዬ ወዬ |
| እኽሊየ እኽሊ፡ እኽሊ፡ | እህል እህል እህል |
| ሲሶ መልክዕ ክልተ ኢድ ሐይሊ | ሲሶው ለመልክ ሁለት እጁ ለሃይል |
| ወዲ አዳም ጠፍአ ንዓኻ ክደሊ | የሰው ልጅ አንተን ፍለጋ ይጠፋል |
| እኽሊ ደቂቅ እኽሊ ደቂቅ | እህል ደቂቅ እህል ደቂቅ |
| አንተሰአንካያ ጅማትካ ትሽ ምቅቅ | ብትጣጣ ጅማት የምት ሽመቀቅ |
| ብዘይ ሕማም ሐይልኻ ተድቅቅ | አለህመም ሃይልን የምታደቅ |
| ብዘይ ንጉስ ዓድኻ ተልቅቅ | አለ ንጉስ አገርን የምታስለቅቅ |

እንዲሁም በአንድ ወቅት በአክሱም አውራጃ የከብት በሽታ (ደስታ) ገብቶ ከብቶቹን ጨረሳቸው ። በዚህ ምክንያት ከብቶች ያለቁበት አንድ ገበሬ እንዲህ ሲል በምሬት አለቀሰ ።

| | |
|---|---|
| (20) ወየ ወየ ወየ | ወዬ ወዬ ወዬ |
| ጉልሐየ ጉልሐየ | ደስታ ደስታ ደስታ |
| ምስ ዝራብዐይዶ አይነበርኩን ምስ ተስታየ | ባለ ወይፈን ባለበሬ አልነበ ርኩም ወይ |
| እዚአ አልቂሰ ናብ ስደተየ | ይችን አልቅሸ ወደ ስደቴ |
| መስሐቅ ሰብ ገበርካኒ ምስ ደቂ ሐወቦየ | የሰው መሳቅያ አደረግከኝ የጠ ላቶቼ |

ይህንን አልቅሶ ወደ ስደት ሄደ

## 1.2.4 ልዩ ልዩ

አልቃሾች በለቅሶ አጋጣሚ የሚያስተላልፉዋቸው መልእክት መካከል ስነምግባር ፣ እምነት ማጉደልን ፣ ክህደትን ፣ ተንኮልን ወዘተ የመሳሰሉ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ይገኙባቸዋል ። በለቅሶአቸውም አጥፊውን ይመክራሉ ተንኮለኛውን ያጋልጣሉ ።

አቶ ወልደማርያም ገብራይ የሚባሉ ሰው በአካባቢያቸው ሰው ሲሞት ቀብር አይሄዱም ነበር አሉ ። አንድ ጊዜ ግን የወንድማቸው ልጅ ይሞትና ወደ ቀብሩ ይሄዳሉ። በዚህ ወቅት አንዲት አልቃሽ አየቻቸውና ወደ መሀል ገብታ እንዲህ ብላ ገጠመችባቸው ።

| | |
|---|---|
| (21) ወየ ወየ ወየ | ወዩ ወዩ ወዩ |
| ከመይ ኢልኩም ወዓልኩም | |
| አይተ ወለማርያም ገብራይ | እንዴት ዋሉ አቶ ወልደማር<br>ያም ገብሬ |
| ሰብ እንትሞትዶ ይፅመድ<br>ብዕራይ | ሰው ሲሞት ይጠመዳል ወይ<br>በሬ |
| ሎምስ ርኢና እንኤና ከይድገም<br>ዳሕራይ | ሌላ ጊዜ እንዳይደግሙ አይተ<br>ናል የዛሬ |

ፊታውራሪ ሐጎስና ደጃዝማች ተሰማ የተባሉ ጥለኞች ነበሩ ። አንድ ቀን ፊታውራሪ ሐጎስ እንድንታረቅ ማይ ፅዩቅ በተባለች ቦታ እንገናኝ ብለው ሽማግሌ ላኩባቸው ። ደጃዝማች ተሰማም በነገሩ ተስማምተው በቀጠሮ ቀን ወደ ቦታው ሄዱ ። ፊታውራሪ ሐጎስ ግን ወደ ቦታው ሲሄዱ አሽከራቸውን "ሲጠጋኝ አነጣጥረህ ግደለው" ይሉታል ። ከቀጠሮው ቦታ ሲደርሱ አሽከራቸው እንደተነገረው ተደብቆ ያነጣጥርና ጠጋ ሲሉ ቢተኩስ ጌታውን ይገድላል ። በዚህ ወቅት በቀብራቸው የተገኙ አንዲት አልቃሽ እንዲህ አሉ ፤

| | |
|---|---|
| (22) ወየ ወየ ወየ | ወዩ ወዩ ወዩ |
| ዓርከያ በሉዎም ቃል ኪዳነ | የቃል ኪዳን ጓደኛዩ አሉዋቸው |
| አብ ማይ ፅዩቅያ በልዎም ንጋነ | ማይ ፅዩቅጋ እንገናኝ አሉዋቸው |
| አብ ከብዶም ካሎ ድያነ | ተንኮል እያለ በሆዳቸው |
| አቦይዝጊማ ምስ ለዋህን ኮነ | እግዚአብሔር ግን ከየዋሆች ጋር<br>ሆነላቸው |

በአጼ ዮሐንስ ዘመን መንግሥት የነበሩ ወ/ሮ ገዛችን የሚባሉ አልቃሽ ደጃዝማች ግደይ የሚባሉትን ወንድማቸውን ገድሎ ተደብቆ የነበረውን ሰው ሐተምቲ ከሚባል ቦታ ያዩትና በወቅቱ ባገኙት አጋጣሚ

(23) ቀታሊ ግደይ ሐዲሩ ሐተምቲ | የግደይ ገዳይ ሐተምቲ አደረ
ሪኤ ሰደድኩዎ ዋይ ሰበይቲ | አይቼ ለቀቅኩት ወይ ሴት መሆኔ
ወዮም ገርዓልታ ሰተይቲ | እዚህ ገርዓልታ እንት የሚጠጡ
ዓውሶ ከም አኽልብቲ | እንደ ውሾች
ተቆነንቲ አልባሶ ከም አንስቲ | ሹርባ የሚሰሩ እንደ ሴቶች

ብለው የወንድማቸው ገዳይ በተጠቀሰው ቦታ መኖሩን ይናገራሉ ። በዚህም ወቅት ደጃዝማች ሐጎስ የተባለ ሌላ ወንድማቸው መልእክቱን ይሰሙና ወደተጠቀሰው ቦታ ሄደው የወንድማቸውን ገዳይ ገደሉት ። ወ/ሮ ገዛችንም በሌላ ጊዜ ባገኙት አጋጣሚ እንዲህ ብለው አለቀሱ ፤

(24) ወየ ወየ ወየ | ወዬ ወዬ ወዬ
ፈዳይ ሕነ ሐጎስ ካብ ተወልደ | ተበቃይ ሐጎስ ከተወለደ
ሕነ ሰኑይ ሰሉስ ካብ ተፈረደ | የሰኞ ብድር ማክሰኞ ከተከፈለ
በኺናዋ ብኽያ ሰብ ግደ | እኛስ አልቅሰናል አልቅሱ ተረኞች
ርእሰይ ደሞ ክቁነና አዋሂደ | ልሰራው ወይ ፀጉሬን አሳምሬ

በአካለ ጉዛይ አውራጃ በናኹዓ በተባለ መንደር አንድ ሹም ነበሩ ። ብዙ ጠላቶች ነበሩዋቸው ። የሹሙ ወንድም ምስጢር እያወጣ ለጠላቶቻቸው እየነገረ ስላስቸገራቸው ሹሙ ወንድማቸውን ይገሉታል ። በቀብሩ ወቅት አንድ አልቃሽ ፤

(25) ወየ ወየ ወየ
አብ ናኹዓ ካብ ተፈጠረ ጋላ | በናኹዓ ከተፈጠረ ገዳይ
ወይ ንሕሰበላ ወይ ንልቀቅላ | ወይ እናጥፋ ወይ እንልቀቅለት

ብሎ በመግጠም ህዝቡን ሹሙን ለመግደል እንዲዘጋጁ አደረገ ። ሹሙም ይህንን ሰምተው አልቃሹን አስጠርተው ሊገድሉት ሲሉ ለግዜው እንዲምሩትና በሁለተኛው ቀብር እንደሚያስተካክለው ቃል ገብቶ ይለቀቃል ። በሁለተኛው ቀብር

(26) ወየ ወየ ወየ | ወዬ ወዬ ወዬ
አንታ እንታይ እዩ እዚ የማናይ ዝስጉደም | በቀኝ በኩል ያለው ያኮረፈው ለምንድነው?
አንታ እንታይ እዩ እዚ ፀጋማይ ዝስጉደም | በግራ በኩል ያለው ያኮረፈው ለምንድነው?
አንታ እንታይ እዩ እዚ ዳሕረዋይ ዝስጉደም | የኋለኛው ያኮረፈው ለምንድነው?
አንታ እንታይ እዩ እዚ | የፊተኛው ያኮረፈው ለም

| | |
|---|---|
| ቀዳማይ ዝስጎደም | ንድነው |
| ዘይዋ'ልተኦም ዋልታ መን አው ሒዶም | ጋሻቸውን እንጂ የማን ጋሻ ቀነሱ |
| ዘይሓዎም ሓው መን አው ሒዶም | ወንድማቸውን እንጂ የማንን ወንድም ቀነሱ |
| ጽንዓት ይሃብኩም ኢሎም ግዳ ዘይኸዱ ዓዶም | ያጥናችሁ ብለው ለምን አይሄ ዱም አገራቸው |

ብለው እንደአለቀሱ ቀባሪውም 'እውነቱን ነው' ብሎ አመጣጡን ለውጦ አለምንም አምባጓሮ ያመጣውን ጦር ፣ ጎራዴ ፣ ሰይፍ ወዘተ ይዞ ወደ የቤቱ ተመለሰ ።

ሁለት ጎረቤት የሆኑ መንደሮች ደግሞ በየጊዜው አምባጓሮ እየ ፈጠሩ ይራበሹ ነበር ። በአንድ የቀብር አጋጣሚ የአንደኛው መንደር አልቃሽ ከብቶቻችን ተሰረቁብን ብሎ በቀብሩ እንዲህ ሲል አለቀሰ ፡—

(27) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| እልበዓል ጉባይ እልበዓል ፋኑስያ | እነ ጉባይ እነ ፋኑስ |
| እልበዓል ጭላይ እልበዓል መስቀላ | እነ ጭላይ እነ መስቀላ |
| እልበዓል ብሩኽ እልበዐል ዳዕሮ | እነ ብሩክ እነ ዳዕሮ |
| እላሕምና ዝመስላ ፅቡቃት ኮማር | ላሞቻችን የሚመስሉ ቆንጆ ኮማሪዎች |
| አብዑርና ዝመስሉ ፅቡቃት ፈካሮ | በሬዎቻችን የሚመስሉ ጥሩ ፈካሪዎች |
| እንዳማርያም ወሲዶመን በብ ምዕሮ | እንዳማርያም ወሰዱዋቸው ቀስ በቀስ |

ብሎ የእንዳማርያም መንደር የሰረቁባቸው መሆናቸውን ሲናገሩ ከእን ዳማርያም ወገን የሆነ አንድ አልቃሽ ደግሞ የሚከተለውን መልስ አቀረበ ፡

(28፡) ወየ ወየ ወየ

| | |
|---|---|
| እንታይ ዝአመሰለ ወግዒ እዮም ዘውግዑ | እንዴት ያለ ወሬ ነው የሚ ያወሩት |
| አይ እንዳማርያምንዶ ባሩ ኸታይ ዘብልኡ | እንዳማርያም አይደሉም እንዴ ባሩካዎችን የሚያበሉት |
| አይ እንዳማርያምንዶ ሕሰታይ ዘብልኡ | እንዳማርያም አይደሉም እንዴ ሕሰታዎችን የሚያበሉት |

| | |
|---|---|
| አይ እንዳማርያም እንዶ ሃዘሞ | እንዳማርያም አይደሉም እንዴ |
| ታይ ዘብልኡ | ሃዘሞዎችን የሚያበሉ |
| ንው እንተብልኩም ሕዚ እን ዶሞ ንው | እስኪ ጠጋ በሉ እንግጠም ካላችሁ |
| ክንቀብር መጺናስ ክትዋቅዑ | ልንቀብር መጥተን ትደባደባ ላችሁ |

በዚህም ጊዜ አምባጓሮ እንዳይነሳ በማለት የሁለቱ አገር (መንደር) ሽማ ግሌዎች አልቃሾቹን በመገሰጽ ቀባሪው ወደየመጣበት በሰላም እንዲ መለስ አደረጉ ።

በትግርኛ የለቅሶ አጋጣሚ የሚተላለፉ መልእክቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም ። ነገሩን ገረፍ ገረፍ አድርገን ለማሳየት ሞከርን እንጂ አል ቃሾቹ በዚህ አጋጣሚ በርካታ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ ፣ በርካታ መልእክቶ ችን ያስተላልፋሉ ። ይህ የለቅሶ አጋጣሚ ለኅብረተሰቡ እንደ መገናኛ ብዙኃን መድረክ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል ለማለት ይቻላል ።

## 1.3 ማ ጠ ቃ ለ ያ

ስነቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ የኅብረተሰብ ባህላዊ ቅርስ እንደመሆኑ የአንድ ህብረተሰብ ያለፈና በወቅቱ የነበረውን ማኅበራዊ ፥ ኢኮኖሚያዊ ፥ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ይገልፃል ።

በዚህ ወረቀት ያየናቸው የትግርኛ ተናጋሪ ብኄረሰብ የለቅሶ ግጥሞች የሚያስተላልፉዋቸው መልእክቶች ከላይ የጠቀስነውን መሠረታዊ ዓላማ የሚያጐሉ ናቸው ። ግጥሞቹ ኅብረተሰቡ በፊውዳል ስርአት ጭቆና እንደደረሰበትና ኅብረተሰቡም በየጊዜው ተቃውሞውን ይገልፅ እንደነበር፤ ከውጭ ወራሪ ሀይሎች ጋር ስለ ተደረጉት ጦርነቶችና ፥ ስለተገኙት ድሎች ፤ የተወሰኑ መሳፍንትና መኳንንት ሕዝቡን በመከፋፈል የሚፈጥሩት የእርስበርስ ግጭት እንደ ነበር ፤ በአካባቢው በዝናብ እጥረትና በአንበጣ መንጋ ምክንያት በተደጋጋሚ ስለሚደርሱ ችግሮች በሚገባ ይተርኩልናል ።

በአጠቃላይ ስነቃል በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረው ቦታ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ ፤ ለኅብረተሰቡ የወደፊት እድገት መሠረት ስለሚሆን በየዘርፉ እየተሰበሰበ ለተተኪው ትውልድ መተላለፍ ያለበት መሆኑን ለመጠቆም እንወዳለን ።

## አባሪ

(1) ቄስ አወጣኸኝ ገብረየስ ፣ (1980) ዕድሜ 41 አክሱም አውራጃ ትግራይ ።

(2) አቶ አባይ መዓሾ ፣ (1980) ዕድሜ 60 አድዋ አውራጃ ትግራይ ።

(3) አቶ ብርሃነ ተስፋይ (1980) ዕድሜ 57 አድዋ አውራጃ ትግራይ።

(4) እና(5)አቶ ባይሩ ገ/የሱስ(1980)ዕድሜ 64 መቀሌ ከተማ ትግራይ።

(6) ግጥሙ ብላታ ሃብተስላሴ የተባሉ አልቃሽ እንዳሉት ገልፀዋል ።

(6) አቶገብረሚካኤል ዕሩይ (198)ዕድሜ 76 አክሱም አውራጃ ትግራይ

(7) አቶ ፍስሃ አረድኸኝ( 1976)ዕድሜ 71 አክሱም አውራጃ ትግራይ ። በአክሱም አውራጃ በዓዴት ወረዳ አንድ ግለሰብ ያሉት መሆኑን ተነግሮናል

(8) መልአከ ብርሃን ከበደ መረሰ 1980 ዕድሜ አልተመዘገበም መቀሌ ትግራይ

ወ/ሮ ደባስ የሚባሉ ሴት ያለቀሱት መሆኑን መረጃ ሰጪው ጠቅ ሰዋል ።

(9) ብላታ ዓብደልቃድር (1976) ዕድሜ 36 አክሱም ትግራይ ። በአክሱም አቶ ተስፋ ስላሴ መሐሪ የተባሉ አልቃሽ ያለቀሱት ሲሆን ብላታ ዓብዳልቃድር ይሕደጎ አጥንተው እንደተናገሩት ።

(10) አቶ ፍስሃ አረድኸኝ (1976) ዕድሜ 71 አክሱም አውራጃ ትግራይ ስማቸው ያልተጠቀሱ አንዲት ሴት እንዳለችው ብለው የሰጡን ነው።

(11) 12 ፣ 13ና 14 ፀሀየ ተፈራ "ባህላዊ የትግርኛ ግጥሞች (1962)ዲ-ግ-ፅ ቀነ - ሥ ዩኒቨርሲቲ

(15) መስፍን መንገሻ (1980) ሁሓ እንድርታ ዕድሜ አልተመዘገበም

(16ና17) አቶ ባህሩ ገብረየሱስ (1980)ዕድሜ 64 መቀሌ ከተማ ትግራይ

(18) (ዓለም ግደይ (1980) ሁሓ ወረዳ እንድርታ አውራጃ ትግራይዕድሜ አልተመዘገበም ።

(19) ገብረ ወርቅነህ(1976) "አክሱም ይህ የተለቀሰው በ1951 ዓ/ም ነው በዚህ ዓመተ ምህረት በአካባቢው የአንበጣ መንጋ ሰብሉን ክፉኛ በማጥቃቱ ህዝቡ ለረሀብ ተጋልጦ ነበር ። የተለቀሰውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ከመረጃ ሰጨው ተገንዝበናል

(20) ስሙ አልታወቀም (1980) ከአክሱም አውራጃ ትግራይ የተገኘ

(21) መልአከ ምህረት ገ/ክርስቶስ (1980)ዕድሜ አልተመዘገበም መቀሌ እንድርታ ።

(22) አቶ ዓለም ግደይ (1980 ሁሓ ከተማ እንድርታ አውራጃ ።

(23ና 24) ፀሀየ ተፈራ

(25ና 26) አስመሮም ገ/ሥላሴ (1976) የትግርኛ ስነቃል ጥናት ዘገባ ለስነቃል ሰሚናር የቀረበ (ያልታተመ) የኢ.ት. ቋንቋዎች አካዳሚ

(27ና 28) አቶ ገ/መድኅን ስብሃት (1976) ዕድሜ 64 አክሱም ። 1951 ዓ/ም እንደተለቀሰ መረጃ ሰጪው ተናግረዋል ።

## ዋቢ መፃሕፍት


ባልከው ቸርነት(1974) “የመንዝ የለቅሶ ግጥሞች ጥናት” (ዲ-ማ-ፅ አ. አ. ዩ.

ደስታ ተክለወልድ ፡ (1972) አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ፡) አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ

ፈቃደ አዘዘ (1972) “የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አፋዊ ኪነተ ቃል” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ለሰሚናር የቀረበ)

ማተቤ አያሌው (1972) “ የአማርኛ የልቅሶና ዘፈን ግጥሞች ከጎንደር ክፍላተ ሀገር የተሰበሰቡ ፡» (ዲ - ማ - ፅ) አ.አ.ዩ

ፀሃየ ተፈራ ፡ (1962) ባህላዊ የትግርኛ ግጥሞች (ዲ-ማ-ፅ) ቀ. ኃ. ስ.

Finnegen, Ruti Oral Literature in Africa :Clorenden Press Oxford (1970)